www.ginbot7.org
የግንቦት 7 ድምጽ
የግንቦት 7፤ የፍትሕ፤የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

ሐምሌ 3 2000 ዓም ቁጥር 8

---

# የግንቦት 7 ታላቁ ስብሰባ በ "ይቻላል"ስሜት ተካሄደ

ግንቦት 7፣በዋሽንግተን ዲሲ ያደረገው ስብሰባ በከፍተኛ መንፈስ መካሄዱን ስብሰባውን ይከታተሉ የነበሩ አስተያት ሰጭዎች ገለጹ።
ያለፈው ቅዳሜ፣እኤአ፣ጁላይ 5፣2008 በዋሽንግተን አሜሪካ የሚደረገውን ስፖርታዊ በአል አያይዞ ግንቦት 7 በጠራው ስብሰባ ላይ ቁጥሩ ከ 500 በላይ የሆነ ህዝብ መገኘቱን ስብሰባውን ይከተታል የነበረው ዘጋቢያችን ገልጿ.ከስብሰባው በሁዋላ ያነጋገራቸው ተሰብሳቢዎች በስበሰባው አካሄድ መርካታቸውንና ለግንቦት 7ም ድጋፋቸውን እንደሚሰጡ ገልጸዋል ብሏል። ስብሰባው የተደረገው በስፖርታዊ በአሉ የመዝናኛ ቀን ቢሆንም፣በርካታ ህዝብ የመዝኒያ ዝግጅቱ እና እንግዶችን መሸኘቱ ሳያግደው አዳራሹን ለማጨናነቅ እንደቻለ ተገልጿል።
 ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ስብሰባውን በመምራት፣አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ፣ዶ/ር ግደይ አሰፋ፣አቶ ኤፍሬም ማዴቦና አቶ ሙሉነህ ኢየኤል ተናጋሪዎች ሆነው የቀረቡ ሲሆን አቶ አንዳርጋቸው ስለ ግንቦት 7 አመሰራረትናየፖለቲካ ግብ አስረድተዋል። ዶ/ር ግደይ ደግሞ ግንቦት 7 ስለሚከተለው የትግል ስልት ትክክለኛነት ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን በንግግራቸውም፣ወያኔ በደም የተጨማለቀ ታሪክ ያለውና የከሀዲዎችና የነፍሰገዳዮች ስብስብ በመሆኑ፣ሰላማዊና የአመጽ ትግሎችን ቀላቅሎ በመታገል ማስወገድ ይገባል ብለዋል።

ኣቶ ኤፍሬም ማዴቦ ደግሞ አሁን ስለምንገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ እና ስለፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት እንዲሁም እያንዳንዱ ዜጋ ስላለበት ሀላፊነት በቂ ማብራሪያ ሰጥተዋል።በቅርቡ ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ በመምጣት ግንቦት 7ትን የተቀላቀሉት አቶ ሙሉነህ በበኩላቸው በአገር ውስጥ ሰላለው አሳዛኝ እና አሰፋሪ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ሁኔታ ተናግረዋል።

አቶ ሙሉነህ፣ በአሁኑ ጊዜ ተቃዋሚዎች እንደልባቸው መንቀሳቀስ እንደማይችሉ፣ከእስር በተፈቱበት ወቅት የፈረሙት ወረቀት በመንግስት ተቋማት ላይ ተቃውሞ እንዳያደርጉ የሚያስገድድ መሆኑ፣ለፍትህ ስርአቱ ገለልተኝነት፣ለመከላከያ እና ለደህነት ሀይሉ ነጻነት እንዲሁም ስለፕሬስና ሌሎች የነጻነት ጥያቄዎች ማንሳት ወይም አንስተው ህዝቡን ለማወያየት መሞከር ወንጀል ተደርጎ እንደሚቆጠርባቸውና በምህረት የተነሳላቸው የእድሜ ልክ እስራት ተፈጻሚ እንደሚሆንባቸው ተናግረዋል። አቶ ሙሉነህ አስገዳጅ ወረቀቶችን ፈርመው ሲወጡ ታሳቢ ያደረጉት፣ በወረቀቱ ላይ የሰፈረውን እብሪትና ማስፈራሪያዎችን ተቀብለው፣ በባርነት ቀንበር ውስጥ ለመኖር ሳይሆን፣ በተፈረመው ወረቀት ላይ ለማመጽ መሆኑን ተናግረዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ስምምነቱን ፈርሞ ከወያኔ ጋር እታገላለሁ የሚል ካለ መዘዙ ግልጽ ነው ያሉት አቶ ሙሉነህ፣ መኖር የሚቻለው መለስ ዜናዊ የሚቸረውን ልጓም እርዝመት እየጠበቁና እየተንከባከቡ ብቻ ነው ሲሉ አጠቃልለዋል።

በስብሰባው የውይይት ጊዜ ግልጽ ሆነው ከወጡት ነጥቦች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

- የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፣አፋኝ፣ገዳይ፣ አገር ሻጭ፣ከሀዲና ዘራፊ በመሆኑ ላይ ስምምነት ያለ መሆኑ
- በአገሪቱና በህዝቡ ላይ ያንዣበበው አደጋ በፖለቲካ፣በኢኮኖሚና በማህበራዊ መልኩ የሚገለጽ እና ስለችግሮቹ ብቻ ማውራት በቂ አለመሆኑ፣ቁም ነገሩ ስርአቱን እንዴት ማስወገድ ይቻላል የሚለውን

መወያቱ መሆኑን

- አምባገነኑን መለስ ማስገደድ የሚቻለው የሰላማዊና የአመጽ ትግሎችን አቀናጅቶ መጓዝ ሲቻል ብቻ እንደሆነ
- ትግሉና የሚመሰረቱት ትብብሮች በግፈኛው የመለስ አገዛዝ ላይ ያነጣጠሩ መሆን እንዳለባቸው፤ የትግሉ አላማም ነጻ የሆኑ የፍትህ፣ የደህንነት፣የምርጫ ቦርድ፣ እና ሌሎች ተቋማትን መመስረት መሆኑንና
- እነዚህ ተቋማት በሌሉበት ሁኔታ ምርጫ ማካሄድም ሆነ በምርጫ መሳተፍ ጨዋታ መሆኑ በስብሰባው ላይ የአብዛኛውን ድጋፍ ያገኙ እምነቶች እንደነበሩ ዘጋቢያችን ሲገልጽ የአገሪቱ የፖለቲካ እና የሲቪክ ሀይሎች በሙሉ ተመሳሳይ አቋም እንዲይዙ ማድረግ ፣ይህን ካላደረጉም ህዝብ ድጋፍ እንዲነፈጋቸው ጥሪ ተደርጓል።

የግንቦት7 አላማ ስልጣን ከመያዝ ጋር የተቆራኘ ሳይሆን፣ ዲሞክራሲያዊ ስርአትን ለመገንባት ቅድሚያ ከመስጠት ጋር የተያያዘ መሆኑ፣ የህዝብ ውክልና ሳይገኝ የሚሰሩ ስራዎች በአሁኑ ጊዜ መነሳት አለባቸው ብሎ እንደማያምን፣ በመሆኑም ከስልጣን ጋር በተያያዘ በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የሚነሳውን ውዝግብ ወደ ጎን ትቶ፣ ህዝብን የስልጣን ባለቤት ማድረግ ዋንኛ ግቡ ላደረገ ማንኛውም ዲሞክራሲያው ትብብር ዝግጁ መሆኑን በመግለጽ፣ ተሰብሳቢው ንቅናቄውን በገንዘብ፣ በጉልበት፣በእውቀት እና በሞራል ለመደገፍ ባሳየው ከፍተኛ ተነሳሽነትና በይቻላል ስሜት ተጠናቋል።